## የኤሌክትሪክ ሥራ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

1. **የማሻሻያዉ ዓላማ**

በደረጃ 3 እና ከዛ በታች የተመረቁ እንዲሁም አጫጭር ሥልጠና ወስደዉ ነገር ግን የሥራ ልምድ የሌላቸዉ ሙያተኞች የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ለማግኘት እንዲችሉ እንዲሁም በኢፌዴሪ የሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን አስተባባሪነት ለወጣቶች አጫጭር ሥልጠና በመስጠት በዚህ ዘርፍ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚደረገዉን እንቅስቃሴ ታሳቢ በማድረግ የኤሌክትሪክ ሥራ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መመሪያዉ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ኤሌክትሪክ ሥራ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 1/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ማሻሻያ**

   1/ በኤሌክትሪክ ሥራ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/2011 አንቀፅ 7/4/ ሐ) በነዚህ ዘርፍ በአድቫንስድ ዲፕሎማ ወይም /10+3/፣ ወይም ደረጃ 4፣ ወይም ደረጃ 5 የተመረቀ እና 0 ዓመትና የሥራ ልምድና ከዚያ በላይ ወይም ደረጃ 3/10+2/ 1 ዓመትና ከዛ በላይ እንዲሁም ደረጃ 2 ወይም 10+1 የተመረቀና 2 ዓመት እና ከዛ በላይ የሥራ ልምድ ያለዉ/ያላትና ደረጃ 1 ወይም 6 ወር ሥልጠና ወይም የደረጃ 1 ሲኦሲ/COC/ እና 3 ዓመት የሥራ ልምድ፡፡ የሚለዉ ተሰርዞ በሚከተለዉ ተተክቷል፣

   ሐ) በነዚህ ዘርፍ በደረጃ 1 የተመረቀ/የተመረቀች ወይም አባሪ በተደረገው ሥልጠና ርዕሶች መሠረት ብያንስ 60 ሰዓት ተግባርና ንድፈ ሀሳብ ያጣመረ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥልጠና የወሰደ/ች ወይመ የደረጃ 1 ሲኦሲ/COC/ እና 0 ዓመት የሥራ ልምድ፡፡

4. **መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ መመሪያ በቦርድ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

…………………………

ዶ/ር ፍሬሕይወት ወልደሐና

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ቦርድ ሰብሳቢ

አዲስ አበባ..ሐምሌ..ዘ..ቀን 2012 ዓ.ም.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

## አባሪ- የሥልጠና ርዕሶች

## ተግባር ተኮር 60ሰዓት የህንፃ ላይ ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ሥልጠና

- የሥራ ቦታ ጥንቃቄ
- መሠረታዊ የኤሌክትሪክሲቲ ምንነት
- መሠረታዊ የኤሌክትሪክ መጠኖች
- የኤሌክትሪክ ምልክቶች
- የዳይሬክት ከረንት እና የአልተርኔቲንግ ከረንት መሠረታዊ ልዩነት
- የቢዩልዲንግ ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደንብ (EBCS)
- የእጅ መፍቻና ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የሚያስፈልጉ እቃዎች
- የኤሌክትሪክ ሽቦ አይነቶች እና የሽቦ ውፍረት
- የኤሌክትሪክ ሽቦ አስተሳሰር፣የሽቦ ጫፍ ማዘጋጀት እና የሽቦ አስተሳሰር ዘዴዎች
- የኮንዲዩት መስመር ዝርጋታና መገጣጠሚያ
- የኮንዲዩት አይነቶችና መጠን
- የኤሌክትሪክ ስዊች አይነቶች
- የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ትግበራ
- የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ
- የህንጻ ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ፍተሻ
- በኤሌክትሪክ የሚሠሩ መሣሪያዎችና ብልሽት